**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)**

Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

## እኛነታችንን እንከላከል

እኔነት ስር በሰደደበት ዘመን ተፈጥረናልና እኛነታችንን ለመከላከል ታሪክ ያስገድደናል። ጨለማ በተባለበት ዘመን ተፈጥሮ፣ በወቅቱ ሃያላን መንግሥታት ሐገሬን አላስነካም ብሎ፣ ክቡር ህይወቱን በገዛ ጥይቱ ለኢትዮጵያ ፍቅር ጥማት ጠጥቶ የተሰዋው የአጼ ቴዎድሮስ ታሪክ መነሻችን ነው። የአፄ ምኒልክ፣ የአፄ ዮሐንስ፣ የአሉላ አባነጋ፣ የበላይ ዘለቀ፣ የባልቻ አባነፍሶ፣ የሸዋረገድ፣ የጣይቱ፣ የዘርዓይ ደረስ፣ የአብዲሳጋ ወዘተ የአጥንትና የስጋ ምርግ የሆነች ኢትዮጵያን ታሪክን ታሪክ አድርገው አንድነቷን ለከርስና ለስልጣን ሳይሸጡ አቆይተውልናልና የኩራታችን ምንጭ ናቸው። ሳንፈጠር ተፈጥረው የነበሩት ታላላቆቻችን ለዴሞክራሲ ምስረታ አይከፍሉ መሰዋዕትነት የከፈሉ የትላንት ወጣቶች፣ ለጽናታችው መሰረት የሆነው፣ ተስማምተው ያወጡትን የውስጣቸውን ደንብ በደም በመጠበቃችው እንደሆነ ታሪካቸው ያስተምረናል።

ጥቂቶች ሕጋቸውን በሕገወጥነት ሲያረክሱት፣ በብዙሃኑ አልገዛም ሲሉ ውጤቱ ክፍፍልና ፍርሻ፣ ገመናን ለጠላት ማስጣት እንደሆነ ድርሳናቸውን አገላብጠን፣ የተከሰተውን ችግር በጥሞና መርምረን ተረድተናል።

ድልን ሳይሆን ትግልን እንደውርስ ተረክበናል። እኛ ወጣቶች የሀገርን እና የወገንን የኢትዮጵያን ጣእም ፍለጋ እነሆ እንደጨው ተበትነን ሀገር አልባ እንዳንሆን በሀገር ውስጥም በውጭም ተደራጅተን ትግል ከጀመርን አመታትን እያስቆጠርን ነው።

በኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ከተደራጀን ገና ሶስት ዓመት እንኳ ባይሞላንም፣ የኢትዮጵያን ጠላቶችና ከጠላት ያደሩ ምልምል ጠላቶችን ስላወቅን ተጠይፈናቸዋል። ይዋል ይደር እንጂ አህያ የጅብ ነች እንዳሉት የኢትዮጵያን ጠላቶች ከተጣበቁበት ህልውና ላይ እንደሙጃሌ ነቅሰን እደምናወጣቸው ምንም ጥርጥር የለንም። ሀገራችንን በቁም ለባእድ እየቸረቸረ መቆሚያና መገለጫ ሊያሳጣን የሚቅበዘበዘው የደደቢት ተምቾች የወያኔ ቡድን፣ ዛሬ ደገሞ በውጭ የምንገኘውን ኢትዮጵያዊያን ለማንበርከክና ለማሰገድ ተቋሞቻችን ላይ የተደራጀ የማፍረስ ዘመቻ መያዙን በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የኢሕአፓ ወጣቶች በውል ተረድተናል።

በወያኔ ስር አንበረከክም ያሉ ቤተ ሃይማኖቶችንም ለመቀማት አሰፍስፏል። በዚህም ሳያቆም የኢትዮጵያዊያን እድሮችን፣ ስብስቦችን፣ ወዘተ ባገኘው ቀዳዳና በተገዙለት ከርሳሞች አማካኝነት ለመበታተንና በስሩ ለማስነጠፍ የብር አይነት እየዘራ ይገኛል።

ከሰሞኑ በስደት የሚገኙ አባት እናቶቻችን ታላላቅ እህት ወንድሞቻችን ሳንፈጠር ጀምረውት ዛሬ 29 ዓመት ያደረሱትን መሰባሰቢያ የስፖርት ፌደሬሽናችንን፣ በውስጡ ሆነው ሲቦረቡሩ የነበሩ ብኩርናታቸውን በጭብጥ ምስር የለወጡ አሳፋሪ ግለሰቦች ለእኛ ለወጣቶች ምን እያስተማሩን ነው? ክሕደትን፣ ተገዢነትን፣ ምርኮኝነትን የመሳሰሉ ገብረጠል ክስተቶችን እያሳዩን ነው። ወገንን, ሐገርን በገንዘብ እንደ ይሁዳ መሸጥ ሕጋዊና ባህልአዊ ለማድረግ የሚደረገውን መቅበጥበት እኛ ወጣቶች በጽኑ እንኮንነዋለን።

Joineprpyl@gmail.com office- 202 291 5832 http://eprpyl.com/
www.facebook.com/eprpyl

የኛነት ጉዳይ ነውና በቀላሉ የምንይዘው አይደለም። አያያዙን አይተው ጭብጠውን ቀሙት ይሆናል። ምዕመናን አምስት እና አስር ሺ እያዋጡ ካቋቋሟቸው ቤተክርስቲያናት የአንዳንዶቹን ቁልፍና ማህተም ከያዙት ውስጥ ለወያኔ በእጅ መንሻነት አሳልፈው ለመስጠት የሚጣጣሩትን ከሃዲዎች ገና ተከላክለን ሳንጨርስ፣ እነሆ ላለፉት 29 ዓመታት በሰሜን አሜሪካ ወጣቶች የወገንና የሐገር ፍቅር እንዲያድርብን እያደረገ ያለውን የእግር ኳስና የስፖርት ፌዴረሽን፣ በጥቅሉ የመሰባሰቢያ እና የአንድነት አንባችን የሆነውን ደፍረውታል። የደፈሩትን ሁለትና ሶስት የአላሙዲ እና የወያኔ ተነጣፊ የሆኑ ግለሰቦችን ተንኮል ለመከላከልና፣ ይህን የጋራ ቅርሳችንን ለማስከበር በሚደረገው ትግልም፣ በዓለም ዙሪያ የምትገኙ ወጣቶች ሁሉ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን።

በምንደኞች ኢትዮጵያና ሀሴቶቿ አይጠፉም!
የኢትዮጵያ ተቋሞቻችንን እንከባከብ!
የሰሜን አሜሪካ የስፖርት ፌዴሬሽን 29ኛው ዓመት በዳላስ ከወያኔ በጸዳ መንፈስ ይከበር!

እናቸንፋለን!